MARYLAND FAMILY NETWORK

# ከቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ጋር መኖር

ለቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች የስራቸውን ጉዳይ ለአከራዮች፣ HOAs እና የህግ አውጪዎች እንዲያቀርቡ የሚያገለግል መመሪያ።





# መግቢያ

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከልን ስራ ላይ ማዋል የሚያበረታታ ሙያ ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜያት በኪራይ፣ በቤት ባለቤቶች ማህበራት (HOA) ስምምነቶች ስር የሚጣሉ ክልከላዎች እና የአካባቢ ክለላ ህጎች የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎችን ስራቸውን እንዲዘጉ ወይም ክልከላዎች ወደሌለባቸው ማህበረሰቦች እንዲሄዱ ያስገድዷቸዋል። ይህ ለአቅራቢዎች ስራ ጥሩ ካለመሆኑም በተጨማሪ ቤተሰቦችን በመኖሪያ መንደሮቻቸው ውስጥ ለልጅ እንክብካቤ ተደራሽ እንዳይሆኑ በእጅጉ ይገድባቸዋል።

እነዚህ ክልከላዎች በአብዛኛው የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ካለመረዳት የሚመጡ ናቸው። ስለ ስራዎ በተመለከተ ከአከራዮች፣ **HOAs**፣ ወይም ሌሎች ጋር ሲነጋገሩ እነዚህ አካላት የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ለማህበረሰብ ስለሚጨምሩላቸው ጥቅሞች ላያውቁ ይችላሉ። ይህ መረጃ እነዚህን ውይይቶች አብዝተው እንዲያካሂዱ እና አንዳንድ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይረዳዎታል።

የሜሪላንድ የቤተሰብ አውታረ መረብ/**Maryland Family Network** የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎችን አከራዮችን፣ **HOAs**፣ የአካባቢ ክለላ ቦርዶችን እና ሌሎችን ስለ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ በተመለከተ እንዲያሳምኑና መረጃ እንዲሰጡ ለመርዳት ይህን መመሪያ እንደ መነሻ ነጥብ እንዲያገለግላቸው አዘጋጅቷል። የአካባቢዎ የልጅ እንክብካቤ የድጋፍ ምንጭ ማዕከል ለሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እና ተጨማሪ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነው።



# የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ምንድን ነው?

## የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ምን ይመስላል?

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ በአቅራቢ ማእከል አማካኝነት የሚሰራ የቅድመ ህጻንነት የትምህርት ፕሮግራም ነው። ወላጆች ይህን ቦታ በብዙ የተለያዩ ምክንያቶች ሊመርጡት ይችላሉ፦

1. የቡድን ብዛት መጠን አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ወንድማማች እና እህትማማቾች በተመሳሳይ ቅልቅል የእድሜ ቡድን ውስጥ ሊሆኑ ስለሚችሉ፤
2. ህጻናት በቅልቅል እድሜ መቼቶች ከመማራቸው ተጠቃሚ ስለሚሆኑ፣
3. ህጻናት ከህጻንነታቸው ጀምሮ እስከ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እድሜያቸው ድረስ አንድ ተመሳሳይ እንክብካቤ አቅራቢ ሊኖራቸው ስለሚችል እና የረጅም ጊዜ ቁርኝቶችና የቤተሰብ ስሜት ስለሚፈጥሩ፤
4. ስርዓተ ትምህርቱ ከአንድ ህጻን የግል ፍላጎቶች ጋር የተያያዘ ሊሆን ስለሚችል፤
5. የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማእከል በልጁ የቤት ውስጥ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ሊያቀርብ ወይም በቤት ውስጥ ከሚቀርቡት ጋር ተመሳሳይ ምግቦችን ሊያቀርብለት ስለሚችል፤
6. የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች የራሳቸውን ስራ ስለሚሰሩ ሰዓቶችን፣ ቀናትና ወጪን በተመለከተ እንደ ሁኔታው ሊቀያየሩ ስለሚችሉ፤
7. አቅራቢዎች እና ወላጆች በትምህርት እና እድገት ግቦች ዙሪያ እንደ ቡድን አብረው ሊሰሩ ስለሚችሉ፣ እና
8. የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከሎች ለቤተሰቦች የመኖሪያ ቦታ በቅርበት ስለሚገኙ።

## የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ለሁሉም ሰው ጥሩ ነው

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አስፈላጊ የማህበረሰብ ዕሴት ነው፦

- የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ቤተሰቦችን አስፈላጊውን ስራ እንዲሰሩና ቤተሰባቸውን እንዲያስተዳድሩ ያስችላቸዋል፤
- ቀጣሪዎች ሰራተኞቻቸው ስለ ልጆቻቸው ደህንነትና ጤና በማይሰጉበት ወቅት የበለጠ አስተማማኝና ውጤታማ የሚሆኑላቸው በመሆኑ ምክንያት ከቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ይጠቀማሉ፤
- ጥናቶች በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ዕድሜያቸው ላይ ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤና ትምህርት የሚያገኙ ህጻናት ጤናማና ምርታማ አዋቂ ሰዎች የመሆን እድላቸው የበለጠ እንደሆነ ያረጋግጣሉ፣ እንዲሁም
- ሁላችንም ከጠንካራ ኢኮኖሚና አነስተኛ ማህበራዊ ወጪ ተጠቃሚ ለመሆን የምንተጋ ሲሆን ይህም ህጻናትን በከፍተኛ ደረጃ ጥራቱን ለጠበቀ የልጅ እንክብካቤ ተዳራሽ ከማድረግ ይመጣል።



# ተጨማሪ ጥቅሞች

ምናልባትም አከራይዎ ወይም HOA ያላሰቧቸው ጥቂት ተጨማሪ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማእከላት ጥቅሞች እዚህ ላይ ቀርበዋል፥

## ለነዋሪዎች እና የቤት ባለቤቶች የሚያስገኙት ጥቅም

በእድሜ ትንሽ የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች በሚኖሩበት ተመሳሳይ የአፓርታማ ህንጻ ውስጥ የልጅ እንክብካቤ መኖር በእጅጉ ጠቃሚ ነው። ለዚህ ምክንያቱ የሚከተለው ነው፦

- እጩ ተከራዮች ለስራ የሚያደርጉትን የየዕለት ጉዞ የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት ማራዘም እንደሌለባቸው በማወቅ የበለጠ የኪራይ ስምምነት የመፈረም ፍላጎት ይኖራቸዋል።
- የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች እና አከራዮች ይህን ጥቅም ለእጩ ተከራዮች በጋራ ለመሸጥ አንድ ላይ ሊሰሩ ይችላሉ።

## የመኖሪያ መንደር ቁጥጥር

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ስራ በቀኑ ውስጥ በሙሉ በተደጋጋሚ የህዝብ መገልገያ ቦታዎችን ይጠቀማል። ይህም አጠራጣሪ ተግባርን ለይቶ ለማየት እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሰርጎ ገቦችን ለመግታት ሌላ እይታዎችን ይሰጣል።

## የዘወትር ገቢ

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች የሚኖሩት በሚሰሩበት ቦታ ላይ በመሆኑ ስራቸው ስኬታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ይህም ወደ አስተማማኝ አከራይ እና መኖሪያ መንደር/ነዋሪ ይተረጎማል።

## ጠንካራ ኢኮኖሚ

የልጅ እንክብካቤ የኢኮኖሚያችን አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ወላጆች በመኖሪያ መንደራቸው ውስጥ ጥራቱን ለጠበቀ የልጅ እንክብካቤ ተደራሽ ሲሆኑ ለመስራት እና ክፍያ ለማግኘት ቀላል ይሆንላቸዋል። አከራዮች እና HOAs ለእነዚህ ስራዎች ድጋፍ ሲያደርጉ ኢኮኖሚውን ለማጠናከር እገዛ ስለሚያደርጉ ይህ ሁሉንም ተጠቃሚ ያደርጋል።

## የልጅ እንክብካቤ ጠንካራ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦችን ይገነባል

አከራዮች እና HOAs የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከላትን በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ አቀባበል ሲያደርጉላቸው በዚያ የሚኖሩ ቤተሰቦች ጠንካራ እንዲሆኑ ለማድረግ እና ይህ መንገድ ለቀጣዩም ትውልዶች እንዲቀጥል በማድረግ እገዛ ያደርጋሉ።



# የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከል ጥያቄና መልስ (Q&A)

ብዙ ሰዎች የልጅ እንክብካቤን በምናባቸው ሲስሉ ብዙ ሰራተኞች፣ ብዙ ቤተሰቦች፣ ብሩህ የኒዮን ምልክት እና የተንጣለሉ የመጫወቻ ሜዳዎች ያሉት የንግድ የህጻናት እንክብካቤ ማዕከል እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ወደ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ስንመጣ ደግሞ ሰዎች በአብዛኛው ስለዚህ አያውቁም ወይም እነዚህን ፕሮግራሞች በየቀኑ ማሳለፍ እንደሚችሉ ያስባሉ። ስለ ስራዎችዎ በተመለከተ የሚባሉ አባባሎችን ለመስበር ወይም ስለ ቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ በተመለከተ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ለማስተካከል መዘጋጀት ይኖርብዎታል።

በእነዚህ ውይይቶች ወቅት ሊጠየቋቸው የሚችሏቸው አንዳንድ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፦

## የልጅ እንክብካቤ በቤት ውስጥ መሆን የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

የልጅ እንክብካቤ መካሄድ ያለበት ለቤተሰቦች እጅግ ተደራሽ በሆነ ቦታ ነው። የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከል የመጀመሪያና የቅርብ መኖሪያ በመሆኑ በዚህ አገላለጽ ማዕከሉ በመኖሪያ ቦታዎች ውስጥ ይመሰረታል። ለልጅ እንክብካቤ የተለያዩ አማራጮችን በምናቀርብበት ወቅት ቤተሰቦች ለቤተሰባቸው ልዩ ፍላጎቶች እጅግ ተስማሚ የሆነውን አማራጭ ሊመርጡ ይችላሉ።

## በእንክብካቤ መስጫዎ ብዙ ልጆች ይኖራሉ?

የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አነስተኛ ነው። ሜሪላንድ ውስጥ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከላት ፍቃድ የሚሰጣቸው እስከ ስምንት ለሚደርሱ ልጆች ሲሆን ትላልቅ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከላት ፍቃድ የሚሰጣቸው እስከ 12 ለሚደርሱ ልጆች ከተጨማሪ ሰራተኞች ጋር ነው።

## ፕሮግራሙ ከመኪና ማቆሚያ ቦታዎቻችን ወይም ከመንገዱ ላይ ሰፊ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ይወስዳል?

የመኪና ማቆሚያ ቦታ በአብዛኛው በአከራዮች ወይም HOA ዝርዝር ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ከሚሰጣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው።

- የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከል መኖር ማለት በመኖሪያ መንደሮች ውስጥ የጥቂት ተጨማሪ መኪናዎች መምጣት ማለት ሲሆን ነገር ግን እነዚህ በዋናነት የሚመጡት በስራ ቀኑ መጀመሪያ እና ማብቂያ ላይ እና ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው።
- በብዙ ሁኔታዎች ወላጆች በመኖሪያ መንደራቸው ውስጥ የሚገኙ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞችን ስለሚጠቀሙ ምንም ተጨማሪ የትራፊክ መጨናነቅ አይፈጠርም።
- በፖሊሲዎ ውስጥ ወላጆች የተመደቡ የመኪና ማቆሚያ ነጥቦች ወይም ቦታዎችን ብቻ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በግልጽ ሊያስቀምጡ ይችላሉ።



# ጥያቄና መልስ (Q&A) የቀጠለ

## በአፓርታማ ወይም መኖሪያ ቤት ላይ ጉዳት ቢደርስስ?

አከራይ ወይም HOA በልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ማእከል ላይ ሊፈጠር ስለሚችል የቤት እርጅናና መፋፋቅ ስጋት ሊኖረው ይችላል። የግዛት ደንቦች የእንክብካቤ አቅራቢ ማዕከል በከፍተኛ ደረጃ ጽዳቱን መጠበቅ፣ መጠገን እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን እንዳለበት እንደሚደነግጉ ያስታውሱ። ማወቅ ያለባቸው ነገር ቢኖር፦

- የህጻናት እንክብካቤ ማእከላት የሚያዳልጡ ምንጣፎችን፣ የተጎዱ የኤሌክትሪክ ክፍሎች ወይም እቃዎችን፣ የሚላጥ ቀለምን፣ ወይም የግዛቱን ፍተሻ የማያልፍ ሌላ እርጅናና መፋፋቅን ጨምሮ ከሁሉም የጤናና ደህንነት አደጋዎች ነጻ መሆን ይጠበቅባቸዋል፤ እንዲሁም
- የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ማዕከላቸውን ለወደፊት እና የአሁን ደንበኞች ማራኪ በሚያደርግ መልኩ ጥሩ እይታ እንዲኖረው የሚያደርጉበት የገንዘብ ማበረታቻ ይሰጣቸዋል።

## በጣም የሚረብሽ ድምጽ (ጫጫታ) ይኖራል?

አከራዮች እና HOAs አብዛኛውን ጊዜ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ከፍተኛ ጫጫታ እንደሚፈጥር እና ሌሎች ተከራዮች ወይም ነዋሪዎችን ሊረብሽ እንደሚችል ይናገራሉ። አንዳንድ መውሰድ የሚችሏቸው የቅድመ መከላከል እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- የቤተሰብ እንክብካቤ ማዕከላት የጫጫታ ደረጃን ብዙ አባላት ካሉት ቤተሰብ ከሚሰማ ድምጽ በላይ እንዳይሆን ለማድረግ የሚንከባከቧቸውን ልጆች ብዛት እንደሚገድቡ ያስታውሷቸው።
- ለወላጆች ልጆቻቸውን በሚወስዱበት ወይም በሚያመጡበት ወቅት የድምጽ/ጫጫታ ደረጃዎቻቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው።
- ከቤት ውጭ የመጫወቻ ጊዜን አብዛኛው ነዋሪዎች ከእንቅልፍ ከነቁ በኋላ ወይም በስራ ላይ በሚሆኑበት ወቅት ለማድረግ ያቅዱ።

## ስራዎ የጋራ አገልግሎቶች እና ክፍያዎቻችንን እንዲጨምሩ ያደርጋል?

አከራዮች በቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማዕከል ምክንያት እንደ ውሀ፣ ሀይል፣ ወይም ከማእከሉ የሚመነጭ ተጨማሪ ቆሻሻ ያሉ አገልግሎቶች ወጪዎቻቸው እንደሚጨምሩ ሊናገሩ ይችላሉ። ስጋታቸውን የሚከተለውን በማስታወስ ማርገብ ይችላሉ፦

- አቅራቢዎች ህጻናትን ወይም ልብሶቻቸውን የማያጥቡ በመሆኑ የውሀ ፍጆታው ከሌሎች ነዋሪዎች የውሀ ፍጆታ በላይ እንደማይሆን በመንገር፣
- ሀይል ቆጣቢ እቃዎች ከሌሎች ነዋሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሀይል እንደሚጠቀሙ በመንገር፤
- የአንድ ወይም ሁለት ከረጢት ቆሻሻ መጨመር የቆሻሻ ስብሰባ ወጪዎችን እንደማይጨምር በመንገር።



# ተጠያቂነት እና የመድን ዋስና

## የሆነ ነገር ቢበላሽ ተጠያቂ መሆን አልፈልግም።

የተጠያቂነት ስጋቶች አከራይ ወይም HOA ስለ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ካሉት ስጋቶች ዝርዝር ላይ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ። አከራይ ወይም HOA አደጋ ቢፈጠር ወይም በወላጅ ቅሬታ ቢቀርብ ሊመሰረቱባቸው ስለሚችሉ ክሶች ሊሰጉ ይችላሉ። ሆኖም የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ማእከላት ከአብዛኞቹ ሌሎች ክፍሎች ይልቅ በተሻለ ደህንነታቸው የሚጠበቅና በአግባቡ የሚያዙ ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ የሚከተለው ነው፦

- ሜሪላንድ የልጅ እንክብካቤ ደንቦችን በተመለከተ በአገሪቱ ውስጥ እጅግ ጥብቅ ከሆኑ ግዛቶች መካከል አንዱ ነው። አቅራቢዎች መኖሪያ ቤት ተኮር ፕሮግራም ለማቅረብ የግዛቱን የፍቃድ መስጫ ሕጎች ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ደህንነትን እና በማእከላቸው ውስጥ የሚገኙ ህጻናት አጠቃላይ ቁጥጥርን በተመለከተ ከወላጆች ይልቅ ከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅባቸው ለዚህ ነው።
- የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች በመጀመሪያ ህክምና እርዳታና CPR የተመሰከረላቸው መሆን፣ የሚሰሩ የእሳት ማጥፊያዎችና የጭስ መመርመሪያዎች ያሏቸው መሆን እና በስራ ላይ የዋለ የጽሁፍ የአደጋ ጊዜ እቅድ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል።
- የልጅ እንክብካቤ ማእከላት የቁጥጥር ጉብኝቶችን ጨምሮ ተደጋጋሚ ፍተሻዎች ይካሄዱባቸዋል።
- የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች የወንጀል የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል።

## የሆነ ነገር ቢከሰት በቂ የመድን ዋስትና አላችሁ?

መደበኛ የቤት ባለቤቶች ወይም የተከራዮች መድን ዋስትና እርስዎን ወይም አከራይዎን ከቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ስራዎ ጋር በተያያዘ ሊነሱብዎ ከሚችሉ ጥያቄዎች ለመጠበቅ በቂ አይደለም። በሜሪላንድ ውስጥ ቁጥጥር ለሚደረግባቸው የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ተጨማሪ የተጠያቂነት መድን ዋስትና የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በህግ ይጠየቃል። የተጠያቂነት መድን ዋስትና በዋናነት ለንብረት ጉዳት፣ የግል ጉዳት እና የአካል ጉዳት ሽፋን ይሰጣል።

የራስዎ ቤት ካልዎት በግዛት ሕግ የቤት ባለቤት የተጠያቂነት ፖሊሲ የሚሰጥዎት የመድን ዋስትና ሰጪ ከቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ስራዎች ጋር በተያያዘ በሚያጋጥም የአካል ጉዳት፣ የንብረት ጉዳት ወይም የግል ጉዳት ምክንያት ለሚፈጠር የአቅራቢዎች ተጠያቂነት ቢያንስ $300,000 ሊሰጥዎት ይገባል።

ለልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ስለሚያስፈልግ መድን ዋስትና እና የወጪ ግምቶች የተመለከቱ ዝርዝሮችን ከ የሜሪላንድ የመድን ዋስትና አስተዳደር ላይ ያገኛሉ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት የአካባቢዎን የልጅ እንክብካቤ የድጋፍ ምንጭ ማዕከልን ያነጋግሩ።



# ክለላ፣ ስምምነቶች እና ኪራዮች

## ለስራው ክልል ይከለልልናል?

ክለላ እንዴት አንድ ህንጻ በተወሰኑ ጂኦግራፊያዊ ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል የሚያስተዳድሩ የአካባቢ ህጎች ወይም ደንቦች ስብስብ ነው። እነዚህ ደንቦች ስራው እንደሚሰራበት ከተማ፣ ካውንቲ ወይም ሌላ የወሰን ክልል ላይ ተመስርተው ይለያያሉ። ፕሮግራምዎን ከመክፈትዎ በፊት ሊከለከል ስለሚችል ቦታው ለልጅ እንክብካቤ ማእከሎችዎ ለመስራት የሚፈቅድ መሆኑን ያረጋግጡ። በማህበረሰብዎ ውስጥ ስለ ክለላ ደንቦች በተመለከተ ማንን እንደሚያነጋግሩ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም የተወሰነ ደንብ በእርስዎ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ላይ ተፈጻሚ ስለመሆን አለመሆኑ በተመለከተ ግልጽ ካልሆነልዎ የአካባቢዎ የልጅ እንክብካቤ የድጋፍ ምንጭ ማእከል ሊረዳዎ ይችላል።

## ኪራይዎ/የማህበረሰብ ስምምነትዎ ስራውን እንዲሰሩ አያስችልዎትም

አከራዮች በኪራዮቻቸው ላይ ስራዎቹ ከኪራይ ክፍሎች ውጭ መሰራት እንደማይችሉ ሊገልጹ ይችላሉ። HOAs በማህበረሰብ ስምምነቶች ላይ ተመሳሳይ ህጎች ሊኖሯቸው ይችላሉ፣ ነገር ግን አባላት በልዩ ሁኔታ እነዚህን እንዳይካተቱ ለማድረግ ድምጽ ካልሰጡ በስተቀር ህጎቹ በቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም። በአብዛኛው የእነዚህ ፖሊሲዎች ጸሀፊዎች ፖሊሲዎቹን በሚጽፉበት ወቅት የልጅ እንክብካቤ በአእምሯቸው ውስጥ አይመጣም። ጸሀፊዎቹ የልጅ እንክብካቤ ማእከላት እንዴት ከሌሎች ስራዎች ጋር የተለዩ እንደሆኑ እና እንዴት ለጠቅላላ ማህበረሰቡ ጠቃሚ እንደሆኑ አይረዱም። ይህ ህትመት ስለ እነዚህ ልዩነቶች እንዲያብራሩ ይረዳዎታል፣ ነገር ግን አከራዮች ወይም HOAs የሚሉት የመጨረሻ ነገር ስለሚኖራቸው እነዚህን ስምምነቶች ከመፈረምዎ በፊት በጥንቃቄ ያንብቧቸው።

## ህጎቹ እንዲቀየሩ <u>እርስዎ</u> ሊያግዙ ይችላሉ

ቤተሰቦች የልጅ እንክብካቤ በሚኖሩበት ቦታ ማግኘት መቻል አለባቸው። የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤን ከገዳቢ የክለላ ሕግ እና ከገዳቢ ስምምነቶችና ኪራዮች መከላከል አለብን። እነዚህ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤን የሚከለክሉ ወይም በእንክብካቤው ላይ ገደቦች የሚያስቀምጡ ክልከላዎች የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎችን ከሙያ ዘርፉ በማስወጣት ሙያውን ያዳክማሉ። ይህም ወላጆችን መክፈል የማይችሏቸውን አማራጮች እንዲጠቀሙ ከማስገደድ በተጨማሪ ለልጆቻቸው ደህንነቱ ያልተጠበቀ እንክብካቤ እንዲመርጡ ሊያስገድዳቸው ይችላል።

ተወካዮችዎን የተስፋፋ የልጅ እንክብካቤን ለሁሉም ቤተሰቦች ተደራሽ ማድረግ ለሁሉም የሜሪላንድ ነዋሪዎች ጠቃሚ እንደሆነ እንዲያውቁ እንደሚያደርጉ ተስፋ እናደርጋለን። ይህ መመሪያ ለጥያቄዎቻቸው መልስ እንዲሰጡ የሚረዳዎ ቢሆንም እባክዎ ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለግዎ እኛን ያነጋግሩን። በተጨማሪም ስለ MFN የህዝብ ፖሊሲ ጥረቶች ከ *marylandfamilynetwork.org* ላይ ሊያውቁ እና ለህዝብ ፖሊሲ ማንቂያዎቻችን ሊመዘገቡ ይችላሉ።

MARYLAND FAMILY NETWORK